# ከነጋሪት ራዲዮ እቅድ እስከ ኢሳት - ለምን እና  እንዴት?

እንደምን ሰነበታችሁ?

የዳዊት ጥያቄ እዚህ ፎረም ላይ እንደወጣ፤ ቅድስት የጻፈችው መልእክት ልብ የሚነካ ነበር። የስራ ባልደረቦቻችን እና ወገኖቻችን ምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ የህሊና አይናችንን ከፍተን ብንመለከት ስለ እውነት በራሳችን እናፍራለን።  ስለሆነም መመላለሱ ግዜያችንን እና ጉልበታችንን ወደ አላስፈላጊ ነገሮች ውስጥ ይከታል ብዬ ነበር መልስ ያልሰጠሁት።  ሁሉም ሰው ብቅ ብቅ ማለቱ በጣም ደስ የሚያሰኝ ነው።  በዚሁ ቀጥሉበት።

በዚህ ጉዳይ ላይ የሚከተለውን አጭር መልስ መስጠቱ ግን ለእናንተም ለግንዛቤ ይረዳ ይሆናል እና ከከባድ ይቅርታ ጋር እንድታነቡት እጠይቃለሁ። በእርግጥ በአሁን ወቅት ይህንን ጉዳይ አንስተን መወያየት አይገባንም ነበር። አሁንም የማተኩረው በርእሱ በጠቀስኩት በዋናው ጉዳይ ላይ ይሆናል፤ ሌሎቹ  ነገሮች ሁሉ ትርፍ ይመስሉኛል።

ክብረት የጻፈው ብዙዎቻችሁ የምታውቁት ታሪክ እንጂ አዲስ ነገር አይደለም። ከዚህ ቀደም ጉዳዩ በከፊል በደብተራው እና አሲምባ ድረ-ገጾች ወጥቶ አንብበነዋል። ከዚያም አልፎ በ Indian oceaan newsletter ላይ ወጥቷል። እዛ ላይ ጉራጌው ጋዜጠኛ …  ኦሮሞው (አነጉ) አበበ ወዘተ የሚሉ ሃረጎችም ተጨምረዋል። እኔን ከብርሃኑ ነጋ ለማዛመድ ይመስለኛል ጉራጌው ጋዜጠኛ  ያሉት። ጉራጌ መሆኔን እዛ ላይ አነበብኩ።አባቴ ግን ከሰሜን ሸዋ እንደተወለደ ነበር የነገረኝ።   ጉራጌ መሆን ያኮራል እንጂ አያሳፍርም።

ችግሩ የኛ ነው ካልን በተለያዩ የብእር ስሞች በፈጠራ ጽሁፎች የሰውን ስም እያጠፉ ከማሰራጨት ይልቅ እዚሁ ብንወያይበት መፍትሄ ለማግኘት ይቀል ነበር።  ባለፉት 3 ሳምንታት እንኳን እዚህ የምንወያይባቸውንና የምንለዋወጣቸውን ሰነዶች ወደ ውጭ ተልከው አይቻለሁ። ይህ ደግሞ ከባድ የስነ-ምግባር ጉድለት ነው።

አብዛኞቻችሁ እንደምታስታውሱት የአምስተርዳሙ የጋዜጠኞች ኮንፈረንስ እንዳለቀ ነጋሪትን ራዲዮ ለመስራት ሃላፊነቱ ለተጠቀሱት አራት ሰዎች ተሰጠ። ፕሮጀክቱ እውን እንደሚሆን ካረጋገጥን በኋላ ስራውን እያጣደፍን ሳለን አንድ ሃሳብ በክብረት በኩል መጣ።

> "የነጋሪት ራዲዮ ዳይሬክተር እኔ ክብረት መኮንን መሆን አለብኝ። ይህ ካልሆነ አጋር ድርጅቱ  PRESS NOW ማናጀር ሚ/ር ዊልኮ አልተባበርም ብሏል።"

ሲል አስደነገጠን።  በዛ ሰዓት መዋቅሩን እየሰራን ስለነበር በጉዳዩ አላሰብንበትም ነበር። ክብረት ግን መዋቅሩ ላይ ዳይሬክተር የሚለው ስር የኔ ስም ካልተጻፈ ሲል አጥብቆ ተከራከረ።  መዋቅር ላይ ስም መጻፍ ያልተለመደ አሰራር እንደሆነ በየተራ ብናስረዳውም አሻፈረኝ አለ።

በወቅቱ የነጋሪት ፕሮጀክትን ስራ እንዲያስፈጽም የወከልነው ክብረት መኮንንን ነበር። ከድርጅቶችም ፤ ከተለያዩ ሰዎችም ጋር  እየተገናኘ ጉዳዮችን እንዲያስፈጽም ሃለፊነት ሰጥተነዋል። ከዊልኮ (ደላላው) ጋር ምን እንዳወሩና እዚህ ውሳኔ ላይ እንደደረሱ አናውቅም።

ይህንን የክብረት ሃሳብ በቃለ-ጉባኤ ላይ ካሰፈርን በኋላ በመርህ ደረጃ እንዲህ አይነቱን አሰራር እንደማንቀበለው እና የተቋቋመው ቦርድ ወደፊት በጉዳዩ እንዲወስንበት ስንል ተስማማን።

ክብረት በውሳኔው አልተስማማም።  እንደውም ካሁን ወዲህ ከእናንተ ጋር አልሰራም ሲል ስብሰባን ረግጦ ወጣ። በሳምንት አንዴ ስናስተላልፈው የነበረው የአምስተርዳም ቴሌቭዥን ፕሮግራምም ተቋረጠ።  በእርግጥ የክብረትን ቤት እንደ ስቱዲዮም ስንገለገልበት ስለነበር የስቱዲዮ እቃዎቹም ሆኑ የሂሳብ ቁጥሩ እዛው ከሱ እጅ ላይ ነበሩ። እስካሁንም እሱ ጋ ናቸው። ይህንን አስመልክቶ የወቅቱ የድርጅቱ ዋና ጸሃፊ አፈወርቅ አግደው በ Nov 7, 2008 የጻፈውን መልእክት ከግርጌ ይገኛል። ሰለ ንብረቱንም ሆነ ስለ ገንዘቡ እስካሁን ምላሹን አላገኘንም።

እዚህ ላይ ቀጥ ብለን ቆመናል -  አላንቀሳቅስ ያለን አንደኛው ችግር።

ሁለተኛው ችግር የአውሮፓ ህብረት ሎቢ ማድረግ እና የነበረው ተስፋን ይመለከታል።   በክብረት ጽሁፍ እንደተገለጸው ያንን ሃላፊነት የወሰድኩት እኔ ነበርኩ። ዳኛ ወልደ ሚካኤልን፤ መስፍን አማንን እና አበበ ቦጋለን ያካተተ የሎቢ ቡድን ከፍተኛ ርብርብ ካደረገ በኋላ የአውሮፓ ፓርላማ ውሳኔ አስተላለፈ። በተለይ በአና ጎሜዝ ከፍተኛ ድጋፍ የአውሮፓ ፓርላማ ለኢትዮጵያ የኢሌክትሮኒክስ ሚድያ ድጋፍ ይሰጥ የሚል መግለጫ ወጣ። ይህንንም በወቅቱ ለነጋሪት ቦርድ

አሳወቅኩ። ቦርዱም አፈጻጸሙ ላይ እንድንቀጥልበት እንደገና ጠየቀን። ... ጉዞ ወደ ብራስልስ። በነገራችን ላይ ይህንን ሁሉ ሳደርግ ስራዬን እየተውኩ እና ወጪዎቹን ሁሉ ከኪሴ እየሸፈንኩ ነበር። እንደተባለውም እዚህ የሚመጡ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችም ሆኑ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ስለ ሜዲያ ሎቢ እንዲያደርጉልን አውሮፓ ህብረት እና ኮሚሽን ቀጠሮ እያስያዝን ወስደናቸዋል።

በመጨረሻ ጉዳዩ ፈንድ ወደሚፈቅደው ኮሚሽን አካል ተመራ። በቀጠሮ ዋናውን ኮሚሽን አግኝተን አነጋገርነው።

ብዙ ከተወያየን በኋላም የአውሮፓ ህብረት ለነጻ ሜዲያ ተብሎ የተያዘ በጀት እንደሌለው ነገረን። ነገር ግን በ Human Rights and Democratization ስም በአመት 20 ሚሊዮን በጀት ለታዳጊ ሃገሮች እንዳለ ይህንንም በመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት ማስፈጸም እንዳሚቻል ፍንጭ ሰጠን።

ይህንኑ እንደገና ለነጋሪት ቦርድ አሳወቅኩ። በጀቱን በ democratization ስም አስፈቅደን በሬድዮ ተግባራዊ እናድርግ የሚል ሃሳብም አቀረብኩ። ቦርድ ውስጥ ከነበሩት በተለይ ሁለቱ የደች ተወላጆች ይህንን ክፉኛ ተቃወሙት። ፕሬስ ናው የሚባለውም አጋር ድርጅት እኛ የቆምነው ለነጻ ፕሬስ ስለሆነ ከዛ ውጭ ያለው ከመርሃን ጋር ይጋጫል ሲል መልስ ሰጠ።

አሁን ሁለት አጣብቂኝ ውስጥ ገብተናል። በሌላ በኩል ደግሞ ቃል በገባነው መሰረት ህዝቡ ከኛ አንድ ነገር እየጠበቀ ነው። እስር ላይ ከነበሩት ሳይቀር የሚያስጨንቁ መልእክቶች ይደርሱናል።

ተሰብስበን አማራጮች ላይ ከተወያየን በኋላም ነጮች የሌሉበት ሌላ የሜዲያ ታስክ ፎርስ ከ800 ኢሮ በላይ ከኪሴ በማውጣት አቋቋምን (TEDH)። ለነጋሪት ራዲዮ በአቶ ከፋለ ማሞ ተሰርቶ የነበረውን ፕሮጀክት ፕሮፖሳልም አሻሽለን አውሮፓ ኮሚሽን አስገባን።

ይህን ግዜ ነው Indian Ocean Newslater ከአውሮፓ ኮሚሽን የተጠየቀው 1.2 ሚሊዮን ኢሮ ለጦር መሳርያ መግዣ እንጂ ለሜዲያ አይደለም ሲል አንድ ጽሁፍ ያወጣው።

ወያኔም ይህንን ሲሰማ ሁለት ሎቢስቶችን ከDLA Piper በሩብ ሚሊዮን ዶላር ውል ብራስልስ ላይ ቀጠረ። ከዚያ በኋላ ነገሮች ሁሉ ከበዱ። ... አጥፍቶ መጥፋት። እዚህ ላይ ሁሉም ነገር ቆመ!

ከሁለት አመት በኋላ በሃገራችን የሜድያው አፈና ያሳሰባቸው ወገኖች የቴሌቭዥን ፕሮጀክት ነድፈው ጥናቱን ከጨረሱ በኋላ 'አዲስ ፈቃድ ከማውጣት ይልቅ TEDHን ለምን አንጠቀምበትም?' የሚል ሃሳብ አቀረቡ። እኛም በአንድ ቅድመ-ሁኔታ ተስማማን። TEDH በነጻ ቦርድ እንዲመራና ቴሌቭዥኑን የሚሰሩት የሜዲያ ሰዎች በሚያቀርቡት ስራ ላይ የኢድቶርያል ነጻነታቸው ሙሉ በሙሉ እንዲጠበቅ። በዚህ ከተስማማን በኋላም ጉዳዩን እዚህ ፎረም ላይ አቅርበን በተለያዩ ጊዜያት ተወያይተንበታል። ውይይቱ ላይ የነበራችሁ ታስታውሱታላችሁ።

ከዚያ ኢሳት ስራውን ጀመረ። የኢሳት ፈንድ የሚገኘው ኢትዮጵያውያን በሚያደርጉት ድጋፍ ነው። ሂሳቡም የሚሰራው እጅግ ፕሮፌሽናል በሆኑ የሂሳብ ባለሙያዎች እና ኦዲተሮች ጥንቃቄ በትሞላበት መንገድ ነው። አንተ እንዳልከው የጥቅም ግጭት ኢሳት ውስጥ የለም። የመዋቅሩ አደረጃጀትም ሆነ አሰራሩ ያንን ፈጽሞ አይፈቅድም። ጥቅም የሚለው ነገር ከየት እንደመታ አይገባኝም። አብዛኞቻችን በነጻ ነው እያገለገልን ያለነው። ሙሉ ሰዓት የሚሰሩትም በራስ ሙሉ ፈቃድ እና በትንሽ የኪስ ገንዘብ ነው - ያለ እረፍት እየሰሩ ያሉት። እንደማንኛውም ድርጅትቶች አንዳንድ አለመግባባቶች ይከሰታሉ: ተከስተውማል። ያንን የውስጥ ችግር ደግሞ የሚፈታ አካል ስላለ ለዚህ መጨነቅ አያስፈልግም።

ኢሳት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የፈጠረው የነጻነት መንፈስ የሚያይ ህዝብ እዚህ እኛ ከምንጨቃጨቅበት ጉዳይ እጅግ ያዝናል። እኔ አንድ ሰው ነኝ። ለዚህ ለተጀመረው ታላቅ ራእይ ችግር ከሆንኩ የማልወገድበት ምንም ምክንያት የለም።

ወደ ነጋሪት ፕሮጀክት ልመለስ። እኔም: አቶ ከፋለም ከነጋሪት ቦርድ ወጥተናል። አፈወርቅ አግደውም የለም። በእኛ ምትክ ሌሎች ታዋቂ ሰዎች ተተክተው ቦርዱን መምራት ጀመሩ። ፈንድ ተገኝቶ ስራ እንደተጀመረ ግን በቦርዱ (ሊ/መንበር) እና በክብረት መሃል ከፍተኛ ችግር ተፈጠረ። ከኛ ጋር ተፈጥሮ ከነበረው የባሰ ችግር።

በ Nov 21, 2008 አዲሱ ቦርድ ግምገማ ላይ ቦርዱ በጻፈው አጭር መልእክት-
"Board members didn't see promising development in order to lunch the radio project. One major problem they identified was that the coordinator's task. They found it out tot be heavy and one person couldn't do it. Kibret couldn't do it satisfactory and he has also admitted that." የሚል መልእክትም ይገኝበታል።

ከኛ ጋር የነበረውም ፍርሃት ይህ ነበር። በአጭሩ የግል (personal) ጉዳይ ሳይሆን የመርህ (principle) ጥያቄ ይመስለኛል። ያንን ሃሳብ ተገድደንም ሆነ ወድደን ብንቀበለው ኖሮ መሃል ላይ ቀጥ ማለታችን አይቀርም ነበር። ሚዛኑ አራት ለአንድ ነው (one against all) ። ከሶስት ሰው ይልቅ አንድ ሰው ትክክል ነው ብሎ የሚያምን እስከሌለ ድረስ።

በመጨረሻ የፕሮጀክቱ ችግር ሁሉ መንስኤ ማን እንደነበር ከስር ያያያዝኩት የኢሜይል (Negarit Board) መልእክት ይነግረናል።

የፕሮጀክቱ እንቅፋቶች እኛ ከሆንን ክብረት መኮንን  ለምን ከሌሎቹ ጋር ተስማምቶ ሊያሳካው አልቻለም?
የሁላችንም ጥያቄ ይህ ነው።

ነጻ የሚያወጣን እውነት ብቻ ነው። እውነትን ካልያዝን ህሊናችንም እረፍት አይኖረውም። እውነት የሚሹ ያገኙዋታል።

# Information request - FEIDIN

**Afework Agedw <aagdew@hotmail.com>** **Fri, Nov 7, 2008 at 6:49 PM**
To: Bogale Kassaye <bogale_kassaye@hotmail.com>
Cc: bogale_kassaye@live.nl, almazbelew74@hotmail.com, s.claus@trouw.nl, wondimu.mekonnen@btinternet.com, ablemma@gmail.com, dadimos@gmail.com

Greetings,

As ex-secretary of the Foundation of Ethiopian Information and Documentation Center in Holland (FEIDIN), I am asking you for information regarding the properties and the money which remained in the account of the foundation.
The foundation had secured 55,000- Euro from several donors for its Ethio-Dutch journalists conference in 2006. Reference to our minutes of meeting on 05/09/2006, there was 20,000 Euro left in the account. As the treasurer, who is register at Chamber of commerce, didn't have the chance to control the balance, we are not able to get the report. In our minutes we had agreed that the 10,000 euro to be saved as a contingency budget and the remaining 10,000 to be used for EthioTV.

ETV has been suspended by the advices of the elders committee, in which you also belong. But we don't have a clue as to where the money is.

We have voluntarily ceased as FEIDIN to form the new foundation FIME. We also want to know if all properties of FEIDIN are transferred to FIME.

Kibret Mekonnen has also bought a laptop and software for editing purposes. Other properties including editing machine, camera and accessories, which was bought by the Ethiopians association are still in the hand of Kibret.

With kind Regards,
Afework Agdew

# Fime

**From: Chris Keulemans** **Wed, Oct 7, 2009 at 6:34 PM**
To:

FIME & Kibret Mekonnen joint statement

Amsterdam, April 5th, 2009
FIME and Kibret Mekonnen part

It is with regret that we announce that the board of the Foundation for Ethiopian Information and Documentation in Holland (FIME) and one of its founders, journalist and producer Kibret Mekonnen, have decided to cease the cooperation in developing an independent radio broadcasting initiative for and by the Ethiopian people.

Mekonnen has contributed greatly to the primary stages of this radio initiative. Working on a voluntary basis, he succeeded in attracting possible partners, funders and contributors. But after developing serious differences of views on policy and organisation, FIME and Mekonnen concluded that, at the moment, there is not a sufficient basis for continuing the cooperation.
FIME will continue the preparations for the independent radio initiative. All organisational, financial and postal matters will be transferred to the board. Mekonnen will continue his professional work as journalist and producer.

Bogale Kassaye, chairman of the FIME board